# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

4ki Diro Kiiro 39

Hawaasa, Ella 8, 2016 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፴፱

ሀዋሳ፣ ሰኔ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም



**Amado**

**Wodhote Kiiro 39/2016**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Saadate Xagichi Doytanno Fande Uurrisate Fultino Wodho Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፴፱/፳፻፲፮**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ ደንብ ገጽ ….**


## WODHOTE KIIRO 39/2016

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Saadate Xagichi Doytanno Fande Uurrisate Fultino Wodho**

Saadate xagichi shiqishonna tuqishsha woyyeessatenni saadate fayyimma agarooshshenna laalchimma lossa hasiisaannota ikkasenni;

Mootimma saadate xagichi hirora gaantanno bajeette addi addi eote hayyonni bowirsatenninna

## ደንብ ቁጥር ፴፱/፳፻፲፮

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ ደንብ**

የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦትና ስርጭትን በማሻሻል የእንስሳት ጤና አጠባበቅንና ምርታማነትን ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከመንግሥት ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ

wirro doyisse horoonsi'ratenni sufishshu noose saadate xagichi shiqishsha qoqqowoho tuqisa hasiissinohura;

Qoqqowu Mootimma Gashshootu Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57 cinaancho quwa 6 garinni tenne wodho fushshino.

1. **Harancho Umo**

   Tenne wodho **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Saadate Xagichi Doytanno Fande Uurrisate Fultino Wodho Kiiro 39/2016"** yine woshshinara dandiinanni.

2. **Qaallate Tiro**

   Qaalu eo wole tiro uysiissannota ikka hoogguro tenne wodho giddo:-

   1. **"Qoqqowo''** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
   2. **"Biiro"** yaa Qoqqowu Mootimma Saadate Jiro Latishshi Biirooti.
   3. **"Mootimmate Saadate Fayyimma Uurrinsha"** yaa qoqqowu mootimma annimmanni galtanno saadate fayyimma owaante uurrinshaati.
   4. **"Saada''** yaa mininna dubbu saada, cea, way giddo saadanna diidu latishsha hanqafanno.
   5. **"Saadate Xagga"** yaa saadate dhibba xagisate woy ittisate woy gargarate horote aana hosanno ayee '*nixire-negere'* woy



የሚመደብን በጀት በተለያየ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎች በማኅልበትና በተደጋጋሚነት እያዘዋዋሩ በመጠቀም አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦት በክልሉ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፯ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሰረት የሚከተለውን ደንብ አዉጥ±ል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ **"የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፴፱/፳፻፲፮"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. **"ክልል"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፤
   2. **"ቢሮ"** ማለት የክልሉ መንግስት የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ነው፤
   3. **"የመንግሥት የእንስሳት ጤና ተቋም"** ማለት በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተቋም ነው፤
   4. **"እንስሳት"** ማለት ለማዳና የዱር እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ የውኃ ውስጥ እንስሳትንና ንብ ልማትን ያጠቃልላል፤
   5. **"የእንስሳት መድኃኒት"** ማለት የእንስሳት በሽታን ለማከም ወይም ለማስታገስ

'*nixirete'* karso ikkanna saadate xagichi uduunne agurranna '*tsere-jarme'* (anti bayotikoota), giddoydinna gobbayiidi irkiraano dhibba sayissanno shiimaadda lubbuwa xaginsanni karsubba, bayolojikaalete gummanna saadate xagishshi uduunne hanqafanno.

6. **"Saadate Xagishshi Uduunne''** yaa saadate dhibba xagisate woy buuxo assate gidoydi woy gobbaydi bisi aana horote aana hosannoha aye uduunnicho ikkanna laboratoore, darre gombanninna koolaansanni uduunne, gombanni kirre, sirinjuwa, marfe, faashsha, fuutta, saniterete uduunnenna rejentoota hanqafannoho.
7. **"Bayolojikaale Guma''** yaa mundeete buuxo; daafurtino woy reytino woy lubbote noo jarmete guma woy '*kittiwaate'* ikkite saadate dhibba gargarate hosannoreeti.
8. **"Jarme''** yaa ayee dhibbi kaima ikkitinnore vayrese, baakiteeriya, fangase, pirotozowa, giddoydinna gobbaaydi irkiraano hanqafannoho
9. **"Baanke"** yaa Itophiyu Daddalu Baankeeti.
10. "**Fande**" yaa jiro woxunninna uduunnunni afi'nanni buichooti.
11. "**Komite**" yaa konne lallawa quwa 8 garinni uuritino saadate xagichi dooytanno fande gashshitanno komiteeti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni

ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገረ ውህዶች ሲሆን ከእንስሳት የህክምና መገልገያ ወይም መሣሪያ በስተቀር ፀረ-ጀርም (አንቲባዮቲኮችን)፣ የውስጥና የውጭ ጥገኞችንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ማከሚያ ውህዶችንና ባዮሎጂካል ውጤቶችን እና የእንስሳት ህክምና መሳሪያ ይጨምራል፤

6. **"የእንስሳት ህክምና መሳሪያ"** ማለት የእንስሳት በሽታን ለማከም ወይም ለመመርመር በውስጥ ወይም በውጭ አካል ላይ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሳሪያ ሲሆን የላብራቶሪ፣ የቀዶ ጥገናና የማኮላሻ መሳሪያ፣ የመስፌያ ክሮችን፣ ስሪንጅዎችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻ፣ ጥጥ፣ የሳኒተሪ መገልገያዎችንና ሪኤጀንቶችን ይጨምራል፤
7. **"የባዮሎጂካል ውጤት"** ማለት የደም ምርመራ፣ የተዳከመ ወይም የሞተ ወይም ህይወት ያለው የጀርም ውጤት ወይም ክትባት ሆኖ የእንስሳት በሽታን ለመከላከል የሚውል ነው፤
8. **"ጀርም"** ማለት ማንኛውም የበሽታ መንስኤ ተህዋስያን ሲሆን ቫይረስን፣ ባክቴሪያን፣ ፈንገስን፣ ፕሮቶዞዋንና የውጭና የውስጥ ጥገኞችን ያካትታል፤
9. **"ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው፡፡
10. ‹**"ፈንድ"** ማለት ሀብት በገንዘብና በዓይነት የሚገኝበት ምንጭ ነው፤
11. **"ኮሚቴ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሰረት የተቋቋመው የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ነው፤

**3. የጸታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው

worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano hanqafannoho.

**4. Fandete Uurrisare**

Sidaamu qoqqowi saadate xagichi doytanno fande (konni gedensaanni "**Fande**" yine woshshinannita) tenne wodhonni uurrinsoonni.

**5. Fandete Hexxo**

Fandete aantete worroonni hexxo heedhannose:-

1. Saadate xagichi shiqishonna tuqishsha ikkado, yannilaanchonna sufishshu noosiha assate;
2. Yanna yannatenni xaggate hirora mootimmate kaaziininni fultanno baajeette ajishate;
3. Saadate xagichi shiqishonni burqitanno fandete eo umose gashshitanno assa.

**6. Fandete Buicho**

Fandete aantete worroonni womaashshu buicho heedhanose:

1. Qoqqowu Mootimma saadate xagichi hirora yanna yannatenni gaantanno bajeette;
2. Mittu mittunku Woradinna Quchumu Gashshooti Amaale Mini gaamanno baajeette;
3. Xagichu hiro aana assinanniti boco fulote gutamanna owaantete baatooshshinni gamba assinanni eo;
4. Irko assitanno bissanni danunninna woxunni afi'nanni kaa'lonni ikkanno.

ሌላኛዉንም ጾታ ይጨምራል፡፡

**4. ስለፈንዱ መቋቋም**

የሲዳማ ክልል የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ (ከዚህ በኃላ "**ፈንድ**" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**5. የፈንዱ ዓላማ**

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦትና ስርጭትን በቂ፣ ወቅታዊና ዘላቂ ማድረግ፤
2. በየጊዜው ለመድኃኒት ግዥ ከመንግስት ካዝና የሚወጣውን የበጀት መቀነስ፤
3. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦት የሚያመነጨው ገቢ ራሱን እንዲያስተዳድር ማድረግ፡፡

**6. የፈንዱ ምንጭ**

ፈንዱ የሚከተሉት ምንጮች ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ መንግስት ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ በየጊዜው የሚመድበው በጀት፤
2. ከእያንዳንዱ ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ከሚመደብ በጀት፤
3. በመድኃኒት ሽያጭ ላይ በሚደረግ የከፊል ወጪ መጋራት እና ከአገልግሎት ክፍያ በሚሰበሰብ ገቢ፤
4. ከለጋሽ አካላት በዓይነት ወይም በገንዘብ ከሚገኝ ድጋፍ፡፡

**7. Fandete Horoonsishsha**

Fande mootimmatenni gaammanni baajeette, saadate xagicho hiratenninna owaantete baatooshshinni afidhanno eo tenne owaantera fannoonni baxxitino baankete akawuuntera gamba assatenninna hasiishshu garinni wirro saadate xagichi hidhora hosiisatenni wirro dooaase sufisatenni saadate xagichi hegeraame shiqisho aana hossanno assinanni. Tittirsha biddissunni gumullanni.

**8. Komite Uurrisannire**

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma saadate xagichi doytanno fande gashshitanno komite (konni gedensaanni "Komite" yine woshshinannita) tenne wodhonni uurrinsoonni

**9. Komitete Miila**

1. Qoqqowu deerrinni komitete aantete worroonni miilla heedhannose:-
   a. Saadate Jiro Latishshi Biiro sooreessi------gambisaancho;
   b. Saadate Fayyimmanna Giwaate Shiqonna Tuqishshi Handaari sooreessi--------borreessaancho;
   c. Saadate Sircho Woyyeessatenna saadate Sagale Handaari sooreessi--------miilla;
   d. Gashshootunna Faynaansete Handaari sooreessi----miila;
   e. Saadate Fayyimma Dayrekitoreete Dayrekitere ----miila;
   f. Faynaansetenna Jajju Gashshooti

**7. ስለፈንዱ አጠቃቀም**

ፈንዱ ከመንግስት የሚመድበው በጀት፣ ከእንስሳት መድኃኒት ሽያጭ እና ከአገልግሎት ክፍያ የሚገኘውን ገቢ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ በተከፈተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ በማጠራቀምና እንደአስፈላጊነቱ መልሶ ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ በማዋል ተዘዋዋሪነቱንና ተደጋጋሚነቱን በማስቀጠል የእንስሳት መድኃኒት ዘለቄታዊ አቅርቦት ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**8. ስለኮሚቴ መቋቋም**

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት መድኃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**9. የኮሚቴ አባላት**

1. በክልሉ ደረጃ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡
   ሀ. የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ----------ሰብሳቢ፤
   ለ. የእንስሳት ጤና፣ ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት ዘርፍ ኃላፊ……ፀሐፊ፤
   ሐ. የእንስሳት ዝርያ ማሻሻልና የእንስሳት መኖ ልማት ዘርፍ ኃላፊ- አባል፤
   መ. የአስተዳደርና የፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ---------አባል፤

Dayrekitoreete Dayrekitere ------miila;

g. Saadate Fayyimma Agarooshshi Dayrekitoreete Ogeessi----miila;

2. Woradu woy quchumu gashshooti deerrinni komitete aantete worroonni miilla heedhannose:-
    a. Saadate jiro latishshi (quchumaho ikkiro giwirinnu) borro mini sooreessi---gambisaancho;
    b. Faynaansete borro mini sooreessi-----borreesaancho;
    c. Saadate fayyimma loosu ha’rinsho qineesaanchi (quchumaho ikkiro saadate jiro latishshi handaari sooreessi) ---miila;
    d. Mittu saadate fayyimma loosu ha’rinsho ogeessi (quchumaho ikkiro qineesaanchu) ------miila;
    e. Mittu faynaansete borro mini hirotenna shallagote ogeessi---miila;

**10. Komitete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Komitete aantete worroonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannose:-

1. Fande aliidimmatenni gashshitanno;
2. Biiro saadate latishsha lainohunni shiqishshano taje safo assi’ratenni uurrinshu keeno assitanno.
3. Jajjunna womaashshu garunni amadamasi buuxxanno;
4. La'anonsa bissa ledo halamatenni fande

ሠ. የእንስሳት ጤና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ዳይረክቴር………አባል

ረ. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይረክቴር………አባል

ሰ. የእንስሳት ጤና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ-----አባል፤

2. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-
    ሀ. የእንስሳት ሀብት ልማት (በከተማ ሲሆን የግብርና) ጽህፈት ቤት ኃላፊ---ሰብሳቢ፤
    ለ. የፋይናንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ--- ጸሐፍ፤
    ሐ. የእንስሳት ጤና ሥራ ሂደት አስተባባሪ (በከተማ ሲሆን የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ኃላፊ)----አባል፤
    መ. አንድ የእንስሳት ጤና ሥራ ሂደት ባለሙያ (በከተማ ሲሆን አስተባበሪ)-----አባል፤
    ሠ አንድ የፋይናንስ ጽህፈት ቤት የግዥና ሂሳብ ባለሙያ------- አባል፤

**10. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. ፈንዱን በበላይነት ይመራል፤
2. ቢሮዉ የእንስሳት ልማትን አስመልክቶ በሚያቀርብዉ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ቋሚ ግምገማ ያደርጋል፤
3. ንብረትና ገንዘብ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፤
4. ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር

tantananno;

5. Fande uurritino hexxo wonshate kaa'litanno womaashshu wolqa ijaarsidhanno gede assitanno.
6. Saadate Jiro Latishshi Borro Mini widoonni saadate xagicho hidhate xamo shiqquro hasiisanno buuxo assatenni woxu fulo ikke hiro jeefinsanni gede assitanno.
7. Kaa’lanotenna addi addi mootimmate bissawiinni danuninni afidhanno saadate xagicho hasiishshu garinni woxu widira soorrite fande bowirsitanno.
8. Fandete jiro hasi’noonni hexxora hosase ha’runsitanno; buuxxanno.
9. Hexxo wonshate kaa’litanno wolootta loossa loossanno.

**11. Komitete Gambisaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Komitete Gambisaanchi:-

1. Komitete gambooshshe woshshanno; massaganno, qineessanno;
2. Komitete muro loosu aana hosase buuxanno;
3. Komitetenna la’annonsa bissara loosu pirogiraame garinni jeefishshu rippoorte shiqishanno;
4. Komite lainohunni ayeeno gambooshshi woy songo aana komite lekkise beeqqanno.
5. Komite uytanno woloota assooteno wonshanno.

ፈንዱን ያደራጃል፣

5. ፈንዱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ የገንዘብ አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፤
6. በእንስሳት ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት አማካይነት የእንስሳት መድኃኒት ግዥ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊነቱን በማረጋገጥ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ግዥው እንዲፈፀም ያደርጋል፤
7. ከለጋሾችና ከተለያዩ የመንግስት አካላት በዓይነት የሚገኝ የእንስሳት መድኃኒትን እንደአስፈላጊነቱ ወደ ገንዘብ ለውጦ ፈንዱን ያጎለብታል፤
8. የፈንዱን ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፡፡
9. ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**11. የኮሚቴ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

የኮሚቴ ሰብሳቢ፡-

1. የኮሚቴዉን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፤ ያስተባብራል፣
2. የኮሚቴ ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
3. ለኮሚቴዉና ለሚመለከታቸዉ በድርጊት መርሀ ግብር መሠረት የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፣
4. ኮሚቴዉን በሚመለከት በማናቸውም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ላይ ኮሚቴዉን በመወከል ይሳተፋል:
5. ከኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

**12. Komitete Borreessaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Komitete Borreessaanchi:

1. Komitete gambooshshi ajanda qixxeessatenni komitetete gambisaanchira shiqishanno
2. Komitete gambooshshi songaale qixxeessatenni miillate shiqishanno
3. Ayee komitete tajubba, mareekkuwanna sanadda amadate yawo noosi
4. Gambisaanchu aanno woloota assooteno wonshanno.

**13. Komitete Gambooshshi Amuraate**

1. Komite sasu aganinni mitte higge uurrinshu gambooshshe assitanno.
2. Uurrinshu gambooshshi ajandi komitete miillara balaxe iillanno assinanni.
3. Wiinama ikkito xaadduro komitete gambisaanchi wiinamu gambooshshe woshshanno.
4. Komitete miilla mereerinni bocu aleenni ikkitannori leelturo gambooshshu guutaho.
5. Komite muro huurote roorrenni sayissanno. Ikkollana huuro lamenkawa taalte beehanturo gambisaanchu huuro uyno gaamoti boordete muro ikkitanno. Ayeeno murote hedo badooshshi songaalete borreessamanno.
6. Konne quwa cinaancho (1) kayse (5) geeshsha worroonniri agaramino gedeenni hee’reenna komite umise gambooshshu amuraate fushshitara dandiitanno.

**12. የኮሚቴ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር**

የኮሚቴ ፀሐፊ፡-

1. የኮሚቴዉን የስብሰባ አጀንዳዎች በማዘጋጀት ለኮሚቴ ሰብሳቢ ያቀርባል።
2. የኮሚቴዉን የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ለአባላት ያቀርባል።
3. ማንኛውም የኮሚቴ መረጃዎች፣ መዛግብትንና ሠነዶችን በኃላፊነት ይይዛል።
4. ከሰብሳቢዉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**13. የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

1. ኮሚቴው በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. የመደበኛ ስብሰባ አጀንዳ ቅድሚያ ለኮሚቴዉ አባላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
3. አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመ የኮሚቴዉ ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
4. ከኮሚቴ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
5. ኮሚቴው ውሣኔውን በአብላጫ ድምጽ ያስተላልፋል፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ያለበት ወገን የኮሚቴዉ ውሣኔ ይሆናል፡፡ ማንኛውም የውሣኔ ልዩነት ይመዘግባል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) እስከ (5) የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**14. Biirote Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Biirote konni worroonni xawinsoonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannose:

1. Komite sayissino muro kaima assi’ratenni fandete bajeette milli assitanno;
2. Qoqqowu shiqishanno saadate xagichi hirote hasatto danuninna bikkunni badatenni tittirshshu xawishshanna mixo qixxeesitanno; garimma noosi hirote seeri garinni xaphoomu hiro ha’risanno;
3. Lekkishshunni Woradunna Quchumu Gashshooti fandete womaashsha sayinsannise woyte isilanchimmasi buuxantino saadate xagichi xaphoomu hiro ha’risatenni tuqissanno;
4. Hirame shiqino xagicho woraddate qeechcha fulo assatenni tuqisanno.
5. Woradunna quchumu gashshooti fandete ho’roonsishsha ha’runsitanno; irko assitanno; loosu jeefishshi rippoorte keentanno.
6. Yannillaancho shallaggotenna odiitete qorqorsha ha’rinsanni assitanno; hasiissannota taashshote qaafo adhitanno.
7. Loosu bilchaantera hasiisanno deerrinni biilloonyenna loosu qeechise aaninni gama booce eeliidi tantanora sayisa dandiitanno.
8. Fandete hexxo wonshate kaa'litannota woloota loossano loossanno.

**14. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1. የኮሚቴዉን ውሳኔ በመከተል የፈንዱን በጀት ያንቀሳቅሳል፡፡
2. በክልሉ መንግሥት የሚቀርቡ የእንስሳት መድኃኒት የግዥ ፍላጎትን በዓይነትና በመጠን በመለየት ዝርዝር መግለጫና ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አግባብ ባለው የግዥ ሕግ መሠረት ጥቅል ግዥ ያከናዉናል፡፡
3. በውክልና ከወረዳና ከከተማ አስተዳደር የፈንድ ገንዘብ ሲተላለፍለት አግባብነት ባለው የመንግስት ፋይናንስ ሕግ መሠረት ጥራታቸው የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ጥቅል ግዥ በማከናወን ያሰራጫል፡፡
4. ተገዝተው የቀረቡትን መድሃኒቶች የወረዳዎችን ድርሻ ወጪ በማድረግ ያሰራጫል፡፡
5. የወረዳና ከተማ አስተዳደር ፈንድ አጠቃቀምን ይከታተላል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ይገመግማል፡፡
6. ወቅታዊ የሂሳብና የኦዲት ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
7. ለሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል በተዋረድ ላለ አደረጃጀት በዉክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
8. የፈንዱን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**15. Saadate Jiro Latishshi Borro Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Borrote minira konni worroonni xawinsoonni biilloonyinna loosu qeechi heerannosi:-

1. Komite sayissino muro kaima assi'ratenni fandete bajeette milli assanno;
2. Woradu woy quchumu gashshooti shiqishanno saadate xagichi hirote hasatto danuninna bikkunni badatenni tittirshshu xawishshanna mixo qixxeesanno;
3. Garimma noosi hirote seeri garinni xagichu hiro hojjinni ha'risanno woy lekkishshunni biirote widoonni hirame shiqanno gede assanno.
4. Saadate xagichi boco womaashsu fulo gutammenna owaantete baatooshshi bikka jeefisiisanno; tittirshu jeefishsha wodhotenni murranni.
5. Hirotenninna owaantete baatooshshinni gamba assinoonni woxe yannatenni addi baankete akaawuntera eo assanno.
6. Fandete ho'roonsishshi aganu fiizikaalenna faynaanshaale rippoortubba qixxeessanno; la'annonsa bissara egensiisanno.

**16. Baajeettete Diro**

Fandete baajeette diri mootimmate baajeette dirooti.

**17. Bankete Akkawuunte**

Fandete womaashshi:-

1. Qoqqowu mootimma milli assitannohu biiro

**15. የእንስሳት ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሚቴዉን ውሳኔ በመከተል የፈንዱን በጀት ያንቀሳቅሳል፡፡
2. ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የሚያቀርበዉን የእንስሳት መድኃኒት የግዥ ፍላጎትን በዓይነትና በመጠን በመለየት ዝርዝር መግለጫና ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡
3. አግባብ ባለው የግዥ ሕግ መሠረት በተናጠል ግዥ ይፈፅማል ወይም በውክልና በቢሮው በኩል ግዥ እንዲፈፀም ያደርጋል፤
4. የእንስሳት መድኃኒት ከፊል የወጪ መጋራትና የአገልግሎት ክፍያ ተመኑን ያስፈፅማል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
5. ከሽያጭና ከአገልግሎት ክፍያ የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ በፈንዱ ልዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፡፡
6. ከፈንዱ አጠቃቀም ወርሀዊ የፊዚካልና ፋይናንሻል ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

**16. የበጀት ዓመት**

የፈንዱ የበጀት ዓመት የመንግሥት በጀት ዓመት ነው፡፡

**17. የባንክ ሂሳብ**

የፈንዱ ገንዘብ፡-

1. የክልሉ መንግሥት የሚያንቀሳቅሰዉ ቢሮው በፈንዱ ስም በሚከፍተዉ ልዩ

fandete su’minni fanantanno addi baankete akawuuntera ofollanno;

2. Woradu woy Quchumu Gashshooti milli assannohu Faynaansete Borro Mini su’minni fanantanno addi baankete akawuuntera ofollanno.

**18. Shallagote Tajenna Qorqorsha**

1. Fandennihu shallagote mazigawinna tajete amadooshshi amuraati qoqqowu mootimma faynaansete gashshooti seera harunsinoha ikkanno.

2. Fande shallagotenna woxu ledo xaaddanno tajubba Qoqqowu Qara Odiitere woy Qara Odiiterenni lekkisantanno odiiterootinni diru dirunkunni qorqorsha assiissanno.

**19. Halamate Gadacho**

Ayee qoqqowu mootimma bissa tenne wodho loosu aana hosiisate hasiissanno irko assate gadacho noonsa.

**20. Qoossonna Gadacho Saysa**

Tini wodho fulate albaanni qoqqowu mootimma, woradda woy quchumu gashshooti milli assanna keeshshinohu xagichu eo womaashshinna jiro fandete widira soorrantino.

**21. Jeefishshu Hee’ranosikki Seeranna Assoote**

Tenne wodho ledo kiphi yitannoti ayee wodho, biddissi woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubba lainohunni jeefishshu dihee’ranno.

የባንክ ሂሳብ ይቀመጣል፡፡

2. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የሚያንቀሳቅሰዉ የፋይናንስ ጽህፈት ቤት በፈንዱ ስም በሚከፍተዉ ልዩ የባንክ ሂሳብ ይቀመጣል፡፡

**18. የሂሳብ መዝገብና ኦዲት**

1. የፈንዱ የመዝገብና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የክልሉን መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ የሚከተል ይሆናል፡፡

2. የፈንዱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በክልሉ መንግሥት ዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

**19. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የክልሉ መንግሥት አካላት ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

**20. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ**

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በክልሉ መንግሥት፣ በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ይንቀሳቀስ የነበረ የእንስሳት መድኃኒት ገንዘብና ንብረት ወደ ፈንዱ ተዘዋውሯል፡፡

**21. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎችና አሠራሮች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

**22. Biddissa Fushshate Biilloonye**.

Biiro tenne wodho jeefisiisate hasiissanno biddisuwa fushshitara dandiitanno.

**23. Wodho Loosu Iima Hosanno Yanna**

Tini wodho barra Ella 8, 2016 M.D hanafe wonsinoonnita ikkitanno.

**Hawaasa, Ella 8, 2016 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidanticha**

**22. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮዉ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**23. ደንቡ ሥራ ላይ ስለ ሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ ሰኔ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**